# ለጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ መታሰቢያ

የመድፍ ላንቃ ያልገታው

ያየር ድብደባ ያልፈታው

ሕይወት አካሉን ለሕዝብ የሰጠው

ችግር ቸነፈርን በልማት የተካው

የሐገር የለውጥ ሐዋርያው

መለስ ዜናዊ እርሱ ነው! እርሱ ነው!

ብዙ ጅምር አለህ ብዙ ውጥን አለህ

እረጅም ነው ሕልምሕ ...........

ምንድነው ጉዳዩ እንደወጣህ ቀረህ

ቀና ብለህ እየው የሕዝቡን ጫጫታ

ቀና ብለህ እየው የሕዝቡን ዋይ ዋይታ

ላንተ ያለውን ፍቅር አመኔታ

የእድሜ ገደብ የለው ሁሉን ያሳዘነው

ስንቱ ሲጠብቅህ ወጥተህ የቀረኸው

ሌሊቱን እንደቀን ቀኑን እንደሌሊት ሰርተህ ያሰራኸው

እረፍት የማታውቀው

ለሥራና ለሥራ ብቻ ተፈጥረህ ያደግኸው

ጅምሩ ሳያልቅ ጉዞው ወዴትነው

ጓዳችን ቀና በል መሪያችን ቀና በል

አጽናና ሕዝብህን አይዞህ በል ወገንህን።

ግዛቸው ተፈራ
ከዋሽንግተን ዲ.ሲ.